**አዋጅ ቁጥር ______/2014 ዓ.ም**

**የመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

የመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ____/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ማሻሻያ**

የመንግሥት እና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1/ ከአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 ተራ ፊደል "ለ" ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል "ሐ" ተጨምሯል።

"ሐ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ከግል ባለሀብት ወይም ከውጭ አገር መንግሥት ወይም ከውጭ አገር መንግሥት የልማት ድርጅት ጋር በመሆን በሚያቋቁመው የጋራ ልማት ድርጅት ወይም ኩባንያ የሚያከናውነው የንግድ ሥራ፤"

2. ከአንቀጽ 39 ንዑስ አንቀፅ /2/ ቀጥሎ አዲስ ንዑሳን አንቀጾች /3/፣/4/ እና /5/ ተጨምረዋል።

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ /1/ እና /2/ ቢኖርም ቦርዱ በሁለትዮሽ የመንግሥት ለመንግሥት የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አማካኝነት ወይም ከግል ባለሀብት ጋር በሚደረግ ቀጥተኛ ግንኙነት በተደረሰ መግባባት መሰረት የቀረበ የፕሮጀክት ሀሳብ ቢተገበር ፕሮጀክቱ በፍጥነት ፋይናንስ እንዲያገኝ በማስቻል የሕዝብ አገልግሎት ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲታመንበት በቀጥተኛ ድርድር በመንግሥት እና የግል አጋርነት እንዲተገበር ሊፈቅድ ይችላል።

4/ በቀጥተኛ ድርድር በመንግሥት እና የግል አጋርነት እንዲተገበር ለቦርዱ የሚቀርብ የፕሮጀክት ሀሳብ ከአገሪቱ አጠቃላይ የልማት ዕቅድ እና ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።

5/ የግል አጋር በመሆን የመግአን ፕሮጀክት በቀጥታ ድርድር ለመተግበር ሀሳብ የሚያቀርብ ኩባንያ ወይም የኩባንያዎች ጥምረት የሚከተሉትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ማሟላት አለበት፣

ሀ) ነዋሪ በሆነበት አገር ሕግ መሰረት የተቋቋመና እንደ ኩባንያ የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የመመስረቻ የምስክር ወረቀት እና በተቋቋመበት አገር መንግሥት የተጠቀሰውን ፕሮጀክት እንዲያለማ እና እንዲተገብር ልዩ ድጋፍ ያለው መሆኑን ሲያረጋግጥ፤

ለ) ፕሮጀክቱን ለመተግበር የሚያስችል በማስረጃ የተደገፈ የፋይናንስ አቋም ማሳየት የሚችል፣ በዘርፉ ሶስት እና ከሶስት በላይ ፕሮጀክቶችን በማልማት የቴክኒክ ብቃት እና የሥራ ልምድ ያለው መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) ኩባንያው የሚያቀርበው የፕሮጀክት ሀሳብ የሀገር ውስጥ ባለሀብት ተሳትፎን፣ የአገር ውስጥ ምርት መጠቀምን እና ለኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል መፍጠርን በሚያበረታታ መልኩ የተቀረፀ መሆን ይኖርበታል፤

መ) ኩባንያው ወይም የኩባንያው ሥራ አስፈፃሚ ወይም ዳይሬክተሮች ወይም ከአምስት ፐርሰንት በላይ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የፕሮጀክቱ ሀሳብ በቀጥታ ድርድር በመግአ እንዲተገበር በቦርዱ ከመወሰኑ በፊት ወደ ኋላ በሚቆጠር የአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያላቸው ሪከርድ ከሕግ ተጠያቂነት የፀዳ ሊሆን ይገባዋል፣

ሠ) ኩባንያው ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ ከሚያስፈልገው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ በብድር ለሚሸፈነው የገንዘብ መጠን ከአበዳሪው ወይም አበዳሪዎች የተሰጠ የብድር ፈቃድ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል፤

ረ) ሚኒስቴሩ ተጨማሪ ዝርዝር መመዘኛ መስፈርቶችን በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣

3. **ከአንቀጽ** 40 **ንዑስ አንቀፅ** /6/ **ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ** /7/ **ተጨምሯል።**

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /6/ የተደነገገው ቢኖርም፣

ሀ) በሁለትዮሽ የመንግሥት ለመንግሥት የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አማካኝነት ወይም ከግል ኩባንያ ጋር በሚደረግ ቀጥተኛ ግንኙነት በተደረሰ መግባባት መሰረት በልዩ ሁኔታ በቀጥታ ድርድር በመንግሥት እና የግል አጋርነት እንዲተገበር የሚፈለግ የፕሮጀክት ሀሳብ ያለው ልዩ ጠቀሜታ በመጀመሪያ በተዋዋይ ባለስልጣን እና ሚኒስቴሩ በጋራ ይገመገማል። ሚኒስቴሩም ፕሮጀክቱ ለሕዝብ የሚያስገኘውን ጥቅም ሲያምንበት በፕሮጀክቱ ሀሳብ መሰረት ዝርዝር ቅድመ አዋጭነት ጥናት እና የኩባንያውን የቴክኒክ፣ የፋይናንስ እና የሕግ አቋም መግለጫ በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄነራል እና በተዋዋይ ባለስልጣን በጋራ እንዲዘጋጅ ያደርጋል።

ለ) ሚኒስቴሩ በቀረበው የፕሮጀክት ሀሳብ ላይ የተካሄደውን የቅድመ አዋጭነት ጥናት እንዲሁም የፕሮጀክቱን ሀሳብ ስላቀረበው ኩባንያ የቴክኒክ፣ የፋይናንስ እና የሕግ

አቋም አጠቃላይ መረጃ የሚሰጠውን የኩባንያውን ገፅታ በመገምገም የግምገማውን ውጤት ለቦርዱ ለውሳኔ ያቀርባል።

ሐ) ቦርዱ ሚኒስቴሩ ያቀረበውን የግምገማ ውጤት ሪፖርት መሠረት በማድረግ የፕሮጀክቱ ሀሳብ በቀጥታ ድርድር በመግአ እንዲተገበር ሊወስን ወይም የቅድመ-አዋጭነት ጥናቱ እና የኩባንያው የፋይናንስ፣ የቴክኒክ እና የሕግ አቋም በድጋሚ ተሰርቶ እንዲቀርብ ሊያዝ ወይም የፕሮጀክት ሀሳቡን ሊሰርዘው ይችላል። ሆኖም ቦርዱ ፕሮጀክቱ በቀጥታ ድርድር በመግአ እንዲተገበር መወሰኑ የፕሮጀክቱ ሀሳብ የመጨረሻ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ ለትግበራ ለኩባንያው እንደተሰጠ አይቆጠርም።

መ) ቦርዱ የቀረበለት የፕሮጀክት ሀሳብ በቀጥታ ድርድር በመግአ እንዲተገበር ሲወስን የፕሮጀክቱን ሀሳብ ለተጨማሪ ጥናት ወደ ሚኒስቴሩ ይልካል።

ሠ) የመንግሥትና የግል አጋርነት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በፕሮጀክቱ ሀሳብ ላይ የሚመለከተው ተዋዋይ ባለስልጣን ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት እንዲያከናውን ያደርጋል። በተዋዋይ ባለሥልጣኑ የተከናወነው የአዋጪነት ጥናት ሲቀርብለትም ጥናቱን ይገመግማል። ለዚህ ዓላማ የአዋጁ አንቀጽ 17 እና 18 እንደ አግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ረ) የመንግሥትና የግል አጋርነት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የአዋጪነት ጥናት ሪፖርቱን ለቦርዱ አቅርቦ ጥናቱ ሲፀድቅ ከተዋዋይ ባለስልጣኑ ጋር በመመካከር ለድርድር መነሻ የሚሆን የፕሮጀክት ስምምነት ረቂቅ አዘጋጅቶ ከድርድሩ በፊት መዘጋጀት እንዲችል ሰነዱን ለኩባንያው ይልካል።

ሰ) ድርድሩ ከመጀመሩ በፊት ተደራዳሪ ወገኖች ድርድሩ ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ እና ድርድሩ የሚመራበትን የሥነ - ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ አቅርበው ማስፀደቅ ይኖርባቸዋል።

ሸ) የመንግሥትና የግል አጋርነት ዳይሬክቶሬት ጄነራል እና ተዋዋይ ባለስልጣኑ በጋራ በዚህ አዋጅ መሠረት ድርድሩን ከኩባንያው ጋር ያደርጋሉ።

ቀ) ከኩባንያው ጋር የተደረገው የቀጥታ ድርድር ሂደት በተሳካ ሁኔታ ሲጠናቀቅ የመንግሥትና የግል አጋርነት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የድርድሩን ውጤት ሪፖርት እና ኩባንያው ለፕሮጀክቱ ትግበራ በግል አጋርነት ተቀባይነት ማግኘቱን ለቦርዱ አቅርቦ ያስፀድቃል።

በ) ከፕሮጀክት ኩባንያው ጋር ውል መፈራረምን እና የፕሮጀክቱን ትግበራ ሂደቶች አስመልክቶ የአዋጁ አንቀጽ 34 እና ከአንቀፅ 44 እስከ 68 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

3. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ _____ ቀን 2014 ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**